# የWASHINGTON ግዛት
# የአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ

| | |
|---|---|
| በሚከተለው ጉዳይ ላይ፡- | የዶሴ ቁጥር። የጉዳይ ቁጥር |
| የይግባኝ ባይ ስም፣ | **ማስታወቂያ የ የችሎት ዓይነት (NOTICE OF …)** |
| ይግባኝ ባይ። | ኤጀንሲ፡- የጤና ጥበቃ ባለስልጣን (Health Care Authority)<br>ፕሮግራም፡- የፕሮግራም ስም<br>የኤጀንሲ ቁጥር |

የጤና እንክብካቤ ባለስልጣን (ኤጀንሲ) ወይም የአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ (Office of Administrative Hearings, OAH) ዓባሪ የተደረገውን የችሎት ጥያቄ ተቀብሏል ቀን።

**የእርስዎ ችሎት በሚከተለው ይካሄዳል፡-**

| | |
|---|---|
| **ቀን፡-** | **የችሎት ቀን** |
| **ሰዓት፡-** | **የችሎት ሰዓት የፓስፊክ ሰዓት ወይም የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛው ከተገኙበት ሰዓት በኋላ ወዲያውኑ።** |
| **አካባቢ፡-** | **የስልክ ኮንፍረንስ ጥሪ (ከታች መመሪያዎችን ይመልከቱ)** |
| **ዳኛ፡-** | **የዳኛው ስም** |

እርስዎ ወይም ምስክር የቃል አስተርጓሚ ከፈለጉ፣ ያለምንም ወጪ እናቀርብልዎታለን። የቃል አስተርጓሚ ለመጠየቅ (800) 583-8271 ላይ ወደ OAH ይደውሉ።

> በአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ (Administrative Law Judge, ALJ) በተለየ መልኩ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኤጀንሲው ተወካይ እና የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛው እንዲመለከቷቸው የሚፈልጉትን ሁሉንም ሰነዶች ወይም ኤግዚቢቶች ከችሎቱ ቢያንስ ከአምስት የሥራ ቀናት በፊት ማቅረብ አለብዎት። ሰነዶችን ለመቅዳት እና ለሌሎች ወገኖች እና OAH ውስጥ ላሉ የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ለማቅረብ የኤጀንሲው ተወካይ እንዲያግዙዎት መጠየቅ ይችላሉ። የWashington አስተዳደራዊ ኮድ (Washington Administrative Code, WAC) 182-526-0370።

የችሎት ዓይነት ላይ እንዴት መሳተፍ እንደሚቻል፡-

1. የእርስዎ የችሎት ዓይነት ከመጀመሩ በፊት (800) 583-8271 ላይ ለOAH ይደውሉ እና ለ የችሎት ዓይነት ሊገኙበት የሚችሉትን ስልክ ቁጥር ይስጡ።
2. ለ የችሎት ዓይነት በተያዘለት ሰዓት ላይ፣ እርስዎ በሰጡት ስልክ ቁጥር ላይ ዳኛው ወይም የኤጀንሲው ተወካይ እስኪደውሉልዎ ድረስ ይጠብቁ።
3. ስልክዎ ተቀባይ እንዳለው፣ ሙሉ በሙሉ ኃይል መሙላቱን እና ቢያንስ ለአንድ ሰዓታት ድረስ የሚቆይ በቂ ደቂቃዎች እንዳሉት ያረጋግጡ።

**ይህ ከተቀበሉት ሰነዶች ጋር ለማነፃፀር የሚያግዝዎትን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ምሳሌ ነው።**

4. በግልጽ የሚሰሙበት እና መስማት የሚችሉበት ጸጥ ያለ ቦታ መሆንዎን ያረጋግጡ።
5. የዳኛውን ጥሪ መቀላቀል ላይ ችግሮች ካጋጠሙዎት ወይም ዳኛው ከ የችሎት ዓይነት መጀመሪያ ሰዓት በአስር ደቂቃዎች ውስጥ ካልደወሉልዎ ወዲያውኑ ወደ OAH (800) 583-8271 ላይ ይደውሉ።

በየችሎት ዓይነት ጊዜ እርስዎ መገኘት ካልቻሉ ወይም ሊገኙበት የሚችሉበትን ስልክ ቁጥር ካልሰጡ የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛው በነባሪነት ሊያቆይዎ እና ይግባኝዎን ሊያሰናብት ይችላል። ይህ ማለት **የችሎት መብትዎን ሊያጡ ይችላሉ ማለት ነው**። WAC 182-526-0284።

ዳኛው ጋር በአካል ችሎት ላይ የመገኘት መብት አለዎት። ይህን ለመጠየቅ፣ ከታች በተዘረዘረው ቁጥር ወደ OAH ይደውሉ።

የችሎትዎ ጊዜ ወይም ቀን እንዲለወጥ **ከፈለጉ** በተቻለ ፍጥነት ለኤጀንሲው ተወካይ ይደውሉ። የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛው ሰዓቱን ወይም ቀኑን ለመለወጥ በቂ ምክንያት እንዳለዎት ይውስናል።

በችሎቱ ላይ እራስዎን መወከል ወይም ጠበቃ ወይም ሌላ ማንኛውንም ሰው እንዲወክልዎት መምረጥ ይችላሉ። ጠበቃዎ ለሚያስከፍሉዎት ማናቸውም ክፍያዎች እርስዎ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ።

**አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ከተቀየረ ወዲያውኑ ለአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ ይንገሩ**። ስለ ችሎቱ ማስታወቂያዎችን እና ሌላ ደብዳቤን ለእርስዎ መላክ ልንፈልግ እንችላለን።

የአካል ጉዳት ወይም የስሜት ህዋሳት ችግር ካለብዎ እና ተቋሞቻችንን ወይም አገልግሎቶቻችንን ሲጠቀሙ ማስተካከያ የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ ልናግዝዎ እንችላለን። እባክዎ (800) 583-8271 ላይ ያነጋግሩን።

ስለ መብቶችዎ፣ ምን ይዘው መቅረብ እንዳለብዎ እና ችሎቶች እንዴት እንደሚሰሩ ለማወቅ እባክዎ ዓባሪ የተደረገውን የችሎቶች መብቶች ማጠቃለያን ያንብቡ። የጦር መሣሪያዎች እና ሌሎች አደገኛ መሣሪያዎች በችሎቶች እና በሁሉም የOAH ቢሮዎች የተከለከሉ ናቸው። WAC 10-20-010። ስለ ችሎቱ የደህንነት ስጋት ካለዎት፣ እባክዎ OAH ያነጋግሩ።

ደብዳቤ በሚላክበት ቀን ላይ የሚቀርብ።

በዓባሪነት ተያይዟል፦ የችሎት ጥያቄ<br>የችሎት መብቶች ማጠቃለያ

| **<u>OAH እንዴት ማነጋገር እንደሚቻል፦</u>** | **<u>እንዴት ማነጋገር እንደሚቻል</u>**<br>**<u>የኤጀንሲ ተወካይ፦</u>** |
|---|---|
| Office of Administrative Hearings<br>PO Box 42489<br>Olympia, WA 98504<br>ስልክ ቁጥር፦ (800) 583-8271<br>ፋክስ፦ | የኤጀንሲ ተወካይ ስም<br>የኤጀንሲ ተወካይ አድራሻ<br>ስልክ፦ |

የአገልግሎት መግለጫ (DECLARATION OF SERVICE)

በWashington ግዛት ሕጎች መሰረት በሐሰት የመመስከር ጥፋት በሕግ ተጠያቂነት እንደሚያስከትል እየተረዳሁ ዛሬ ይህንን ሰነድ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ወገኖች ሁሉ እንዳቀረብኩ አውጃለሁ። የተጠናከረ የደብዳቤ አገልግሎቶችን፣ የU.S. ደበዳቤን ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ ኢሜይልን በመጠቀም ለወገኖቹ ቅጂውን ወደ የተመዘገበ አድራሻቸው ልኬያለሁ።

ይህ የችሎት ማስታወቂያ የተላከላቸው ሰዎች ዝርዝር።

ቀን የችሎቱ ማስታወቂያ በደብዳቤ የተላከበት ቀን ላይከተማ፣ Washington።
(በደብዳቤ የተላከበት ቀን)

______________________________________
ተወካይ
የአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ
PO Box 42489
Olympia, WA 98504

**ይህ ከተቀበሉት ሰነዶች ጋር ለማነፃፀር የሚያግዝዎትን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ምሳሌ ነው።**